# ጳጳስ ተዝካር ብላ!



ሰማእታት ቅዱሳን ይኸን ጉድ አላዩ!
እነ አቡነ ጴጥሮስ ይኸን አልታዘቡ፡
አድማሱ ጀምበሬ ይኸንን አልሰሙ፣
ፓትርያሪክ ጳጳሳት ለፋሽሽት ሲሰግዱ።

በበጎቻቸው ደም ስልጣን አስከብረው፣
ተበግ አራጆች ጋር ሲያድሩ ተወባርተው፣
የደመ-ነፍስ ያህል ስግጥጥ እንኳ አይላቸው።

ለሕዝብ መድህንነት ሲሰቀል ጎልጎታ፣
ለራሱ ድሎት ሲል ጳጳስ ሕዝብ አሰዋ።

ጴጥሮስና ጳውሎስ በቄሳር ሲቀሉ፣
የዛሬ ጳጳሳት ሹመት ተቀበሉ።

ተመሐል ደረት ላይ መስቀል አንዠርግገው፣
ተራስ ቅላቸውም ያማረ ቆብ ደፍተው፣
ለአባይ ሲታዘዙ ትንሽ አይከብዳቸው።

ገዳማት ተቃጥለው ባህታውያን ሲያልቁ፣
ፓትርያሪክ ተባይ አቡኑ ጳጳሱ፣
ተአቃጣዮች ጋራ ግብር ይበላሉ።

እንዲናገር ቢያዝዝ ነፍስ እስተንፋስ ያለው፣
የደም የስደት ጎርፍ በዓይን ብረት አይተው፣
ጳጳሳት ጪጭ አሉ በቀፈት ታፍነው።

ተአሕዛብ ተአውሬዎች ሲዋደቅ አማራ፣
ፍታት ፈታሁ እያልክ ጳጳስ ተዝካር ብላ።

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ነሐሴ ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም.